የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 66
ADDIS ABABA - 30th July, 1999

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..ገጽ ፩ሺ፩፻፵፮

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 52/1999
National Veterinary Institute Establishment Council of Ministers Regulations ......................... Page 1146

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፺፩ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩/ (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· መቋቋም

፩· ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት /ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ/የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪· ኢንስቲትዩቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ።

፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግሥት የሚሰየም አካል የኢንስቲትዩቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ።

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 52/1999 COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE NATIONAL VETERINARY INSTITUTE*

*These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.*

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "National Veterinary Institute Establishment Council of Ministers Regulations No. 52/1999."

2. *Establishment.*

1) The National Veterinary Institute (hereinafter "the Institute") is hereby established as a public enterprise.
2) The Institute shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

A body to be designated by the Government shall be the supervising authority of the Enterprise.

፬. ዋና መሥሪያ ቤት፡

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት ደብረዘይት ሆኖ ፤ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል ።

፭. ዓላማ ፡

ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡

፩. ለተለያዩ የእንስሳት በሽታዎች ዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ክትባቶች ማምረት፡

፪. ልዩ ልዩ የእንስሳት መድኃኒቶችን ማቀነባበርና ማዋሃድ ፡

፫. ለምርትና ለእንስሳት በሽታ ምርምር ሥራ የሚያገለግሉ ባዮሎጂካሎችንና ሪኤጀንቶችን ማምረት ፡

፬. ምርቶችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ አቅርቦት በመሸጥ ትርፍና ትርፋማነትን ማሳደግ ፡

፭. በተጨማሪ ሌሎች ተዛማጅ ምርቶችን ማምረት ።

፮. ካፒታል ፡

ለኢንስቲትዩቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፵፭ ሚሊዮን ፯፻፴፯ሺ.፩፻፳፪ (አርባ አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ. አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፵ ሚሊዮን ፩፻፹፱ሺ. ፩፻፳፪ (አርባ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ. አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር) በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል ።

፯. የኃላፊነት ወሰን

ኢንስቲትዩቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ።

፰. ኢንስቲትዩቱ የሚቆይበት ጊዜ ፡

ኢንስቲትዩቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ።

፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ፡

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Institute shall have its head office in Debre Zeit and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. *Purpose*

The purposes for which the Institute is established are:

1) to produce vaccines of international standard for various animal diseases;
2) to formulate and produce different veterinary drugs;
3) to produce biologicals and reagents to be used for production and research on animal diseases;
4) to sell its products in the local and export markets;
5) to engage in other related activities conducive to the attainment of its purposes.

6. *Capital*

The authorized capital of the Institute shall be Birr 45,737,122 (Forty five million seven hundred thirty seven thousand one hundred twenty two Birr) of which Birr 40,189,122 (Forty million one hundred eighty nine thousand one hundred twenty two Birr) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Institute shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Institute is established for an indefinite duration.

9. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force as of the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 30th day of July, 1999.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE